የማቴዎስ ፳ ሴቶች

# ትዕማር

የጥናት መምሪያ

Selah
PAUSE • REFLECT



# መግቢያ

በማቴዎስ ፩ ውስጥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የዘር ሐረግ ውስጥ የአምስት ሴቶችን ስም እናያለን። ለብዙዎቻችን የዘር ሐረግ መቁጠር ከመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን አብልጠን የምንወደው አካል ላይሆን ይችላል። አንዳንዶቻችን ከነጭራሹ ልንዘለው እንችላለን። ሆኖም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘሩት በእያንዳንዱ የዘር ሐረጎች ውስጥ ትኩረትን የሚስቡ አስደናቂ ነገሮችን እናያለን፣ ማቴዎስ ፩ም እንዲሁ ነው።

የሴቶች ወይም የእናቶች ስም በአይሁድ የዘር ሐረግ ውስጥ በተለምዶ አይጠቀሱም። በእውነቱ በአይሁድ ታሪክ ዝና የነበራቸውን ትውልዶች ብቻ በመጥቀስ፣ ሌሎችን በመዝለል የዘር ሐረጎችን በአጭሩ የሚጽፋ ሰዎች ስለነበሩ፣ በዘር ሐረግ ውስጥ መጠቀስ ራሱ በጣም ትልቅ ክብር ነበር። ይህንን ስናስብ እነዚህ አምስት ሴቶች ማለትም ትዕማር፣ ረዓብ፣ ሩት፣ ቤርሳቤህ እና የኢየሱስ እናት ማርያምን ማቴዎስ መጥቀሱ በእርግጥ ሊያስደንቀን ይጀምራል።

እነዚህ አምስት ሴቶች ሕይወታቸው ሲጠና ስለ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ስለ ወንጌል፣ እና ስለ እለት ተእለት ሕይወት የሚነግረን ነገር አለ።

© 2020 by Selah Ethiopia

Published by Selah Ethiopia
P.O. Box 479, Addis Ababa, Ethiopia

Published in Addis Ababa, Ethiopia
All rights reserved. No part of this publication may be reproduced in any form without permission from the publisher, except in the case of brief quotations embodied in other works or reviews.

All Scripture quotations are from the NASV Amharic Bible (Holy Bible, New Amharic Standard Version (Addisu Medebegna Tirgum)) Copyright © 2001 by Biblica, Inc.®
All rights reserved worldwide.

Illustrations
Front cover: Yikunoamlak Ayalew
Back cover: Ammanuel Anbessie

# ስለ ጥናት መምሪያው

የእግዚአብሔርን ቃል ለመረዳት ስንፈልግ መንፈስ ቅዱስ ዋና አስተማሪያችን መሆኑን መዘንጋት የለብንም። ኢየሱስ “መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ነገር ያስተምራችኋል፤ እኔ የነገርኋችሁንም ሁሉ ያሳስባችኋል” ይለናል (ዮሐንስ 14፥26)። በጥናታችን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲያስተምረን፣ እንዲለውጠን ከመጠየቅ ባሻገር የሚከተሉትን ይዘው መዘጋጀት ጠቃሚ ነው ብለን እናስባለን።

- መጽሐፍ ቅዱስ
- ማስታወሻ ደብተር (ሐሳብዎን ለማስፈሪያ ቦታ ስላለው ይህንን መምሪያ አትመው በማውጣት መጠቀም ይችላሉ)
- በመጽሐፍ ቅዱስዎ ወይም በማስታወሻዎ ውስጥ ለመጻፍ ቀለም ያላቸው እስኪብርቶዎች ወይም እርሳሶች

---

በዚህ ጥናት ውስጥ ሁሉ ራስዎን እነዚህን ጥያቄዎች እየጠየቁ ይሂዱ፥

- ይህ ክፍል ስለ እግዚአብሔር ልብ፣ መንገዶች፣ እና ባሕርይ ምን ይነግረኛል?
- ይህ ክፍል ወደ ኢየሱስ እና ወደ ወንጌል እንዴት ይጠቁማል?
- ልከተለው ወይም ላስወግደው የሚገባ ምሳሌ አለ? ከሆነስ፣ ምን ዓይነት ለውጥ ወይም ምላሽ መስጠት አለብኝ?

ተጓዳኙን የጥናት ቪዲዮ መመልከት ጠቃሚ ሆኖ
ሊያገኙት ይችላሉ። ቪዲዮውን ከዚህ በታች ያለውን
ምስል በመንካት ወይም በድህረ-ገፃችን
www.selahethiopia.org/tamar ያገኙታል።




Watch on YouTube

# ዘፍጥረት 38

**ይሁዳና ትዕማር**

1በዚያም ወራት ይሁዳ ከወንድሞቹ ተለይቶ፣ ኤራስ ወደተባለ ዓዶሎማዊ ሰው
ወረደ፤ እርሱም ዘንድ ለመኖር ቤቱ ገባ። 2እዚያም ሳለ፣ ይሁዳ የከነዓናዊውን
የሴዋን ሴት ልጅ አየ፤ እርሷንም አግብቶ አብሯት ተኛ፤ 3እርሷም ፀንሳ ወንድ ልጅ
ወለደች፤ ስሙም ዔር ተባለ። 4እንደ ገናም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙን አውናን
አለችው። 5አሁንም ደግማ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙንም ሴሎም ብላ አወጣችለት፤
እርሱንም የወለደችው ክዚብ በተባለ ቦታ ነበር።

6ይሁዳ የበኵር ልጁን ዔርን፣ ትዕማር የምትባል ሚስት አጋባው። 7የይሁዳ የበኵር
ልጅ ዔር ግን በእግዚአብሔር (ኤሎሂም) ፊት ክፉ ነበር፤ እግዚአብሔርም (ያህዌ)
ቀሠፈው።

8በዚህ ጊዜ ይሁዳ አውናንን፣ “ዋርሳዋ እንደ መሆንህ ከወንድምህ ሚስት ጋር ሩካቤ
ሥጋ በመፈጸም የወንድምህን ስም የሚያስጠራለት ዘር ተካለት” አለው። 9አውናን
ግን የሚወለደው ልጅ የእርሱን ስም የሚያስጠራ እንደማይሆን ስላወቀ፣ ከወንድሙ
ሚስት ጋር ሩካቤ ሥጋ በፈጸመ ቍጥር የወንድሙንም ስም የሚያስጠራ ልጅ
እንዳይወልድ ዘሩን በምድር ላይ ያፈስ ነበር። 10ይህም በእግዚአብሔር (ያህዌ) ፊት
ክፉ አድራጎት ሆኖ ስለ ተገኘ፣ እርሱንም እግዚአብሔር (ያህዌ) በሞት ቀሠፈው።
11ከዚያም ይሁዳ ምራቱን ትዕማርን፣ “ልጄ ሴሎም ለአካለ መጠን እስኪደርስ ድረስ
ወደ አባትሽ ቤት ሄደሽ መበለት ሆነሽ ብትኖሪ ይሻላል” አላት፤ ይህን ያለውም፣
ሴሎም እንደ ወንድሞቹ ተቀሥፎ ይሞትብኛል ብሎ ስለሠጋ ነበር። ትዕማርም
እንዳላት ሄደች፤ በአባቷም ቤት ተቀመጠች።

12ከብዙ ጊዜ በኋላ የሹዓ ልጅ፣ የይሁዳ ሚስት ሞተች። ይሁዳ ከሐዘኑ ከተጽናና በኋላ
ከዓዶላማዊው ከሒራ ጋር የበጎቹን ጠጕር የሚሸልቱ ሰዎች ወዳሉበት ወደ ተምና
ሄደ።

13ሰዎቹም ለትዕማር፣ “ዐማትሽ የበጎቹን ጠጕር ወደሚሸልቱ ሰዎች ዘንድ ወደ
ተምና እየሄደ ነው” አሏት። ይህን እንደ ሰማች 14የመበለትነት ልብሷን አውልቃ፣

ማንነቷ እንዳይታወቅ ፊቷን በሻሽ ተከናንባ ወደ ተምና በሚወስደው መንገድ ዳር
ባለች ኤናይም በተባለች ከተማ መግቢያ ላይ ተቀመጠች፤ ይህን ያደረገችው፣ ሴሎም
ለአካለ መጠን ቢደርስም፣ እርሷን እንዲያገባ አባቱ አለመፈለጉን ስላወቀች ነው።

[15]ፊቷ በሻሽ ተሸፋፍኖ ሲያያት፣ ይሁዳ ዝሙት ዐዳሪ መሰለችው። [16]ምራቱ መሆኗን
ባለማወቁ፣ እርሷ ወዳለችበት ወደ መንደሩ ዳር ጠጋ ብሎ፣ “እባክሽ አብሬሽ ልተኛ”
አላት። እርሷም፣ “አብሬህ ብተኛ ምን ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው።

[17]“ከመንጋዬ መካከል አንድ የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ” አላት። እርሷም መልሳ፣
“ጠቦቱን እስክትልክልኝ ድረስ ምን መያዣ ትሰጠኛለህ?” ብላ ጠየቀችው።

[18]“ታዲያ ምን መያዣ ልስጥሽ?” አላት። እርሷም፣ “የማኅተም ቀለበትህን
ከነማሰሪያው፣ እንደዚሁም ይህን በትርህን ስጠኝ” አለችው። የጠየቀችውን ሁሉ
ሰጣትና አብሯት ተኛ፤ እርሷም ፀነሰች። [19]ከዚያም ወደ መኖሪያዋ ተመልሳ፣ ሻሽዋን
አውልቃ እንደ ወትሮዋ የመበለት ልብሷን ለበሰች።

[20]ይሁዳ በመያዣ ስም የሰጣትን ዕቃዎች ለማስመለስ የፍየሉን ጠቦት በዓዶሎማዊ
ወዳጁ እጅ ላከላት፣ መልእክተኛው ግን ሴትየዋን ሊያገኛት አልቻለም። [21]“በኤናይም
ከተማ መግቢያ ከመንገዱ ዳር የነበረች ያቺ ዝሙት ዐዳሪ የት ደረሰች?” ሲል
ጠየቃቸው። ሰዎቹም፣ “በዚህ አካባቢ እሪ ምንም ዝሙት ዐዳሪ ታይታ አትታወቅም”
አሉት።

[22]መልእክተኛውም ወደ ይሁዳ ተመልሶ፣ “ሴቲቱን ላገኛት አልቻልኩም፤ ነዋሪዎቹም
‘በዚህ አካባቢ እንደዚህች ያለች ዝሙት ዐዳሪ የለችም’ አሉኝ” ብሎ ነገረው።

[23]ይሁዳም፣ “እንግዲህ መያዣውን እንደ ያዘች ትቅር፤ አለዚያ መሣቂያ እንሆናለን።
ለነገሩማ ይህን ፍየል ላክሁ፤ አንተም ፈልገህ አላገኘሃትም” አለ።

[24]ከሦስት ወር ያህል በኋላ፣ “ምራትህ ትዕማር ዘማዊ ሆናለች፤ ከዚህም የተነሣ
አርግዛለች” ተብሎ ለይሁዳ ተነገረው።

ይሁዳም፣ “አውጧትና በእሳት ተቃጥላ ትሙት” አለ።

25እርሷም ተይዛ በምትወሰድበት ጊዜ ለዐማትዋ፣ “እኔ ያረገዝሁት የእነዚህ
ዕቃዎች ባለቤት ከሆነ ሰው ነው” ስትል ላከችበት፤ ደግሞም፣ “የማኅተሙ ቀለበት
ከነማንጠልጠያውና በትሩ የማን እንደሆነ እስቲ ተመልከት” አለችው።

26ይሁዳም ዕቃዎቹን ዐውቆ፣ “ልጄ ሴሎም እንዲያገባት ባለማድረጌ፣ እርሷ ከእኔ
ይልቅ ትክክል ናት” አለ። ከዚያም በኋላ ከእርሷ ጋር አልተኛም።

27የመውለጃዋ ጊዜ እንደ ደረሰም ፅንሷ መንታ መሆኑ ታወቀ። 28በምትወልድበትም
ጊዜ አንደኛው እጁን አወጣ፤ አዋላጂቱም፣ “ይህኛው መጀመሪያ ወጣ” ስትል በእጁ
ላይ ቀይ ክር አሰረችለት፤ 29ነገር ግን፣ እጁን መልሶ ሲያስገባ ወንድሙ ተወለደ።
አዋላጂቱም “አንተ እንዴት ጥሰህ ወጣህ!” አለች፤ ከዚያም ስሙ ፋሬስ ተባለ።
30ከዚያ በኋላ እጁ ላይ ቀይ ክር የታሰረለት ወንድሙ ተወለደ፣ ስሙም ዛራ ተባለ።

# ትዕማር

**ዘፍጥረት 38 | ማቴዎስ 1፥3**
የትዕማርን ማንነት፣ ሕይወት እንዲሁም በወንጌል ውስጥ ስላላት ሚና በጥልቀት ለማጥናት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ይመልከቱ፤ ያሰላስሉ።

**ዘፍጥረት 38፥1-11**

- ይሁዳ ከቤተሰቡ ተለይቶ ከነዓናዊት ሴት ያገባው ለምን ሊሆን ይችላል?

- ያለ ወራሽ ስለ ሞተ ሰው በተመለከተ በአይሁድ ሕዝብ ውስጥ ምን ዓይነት ልማድ ነበር? (ዘዳግም 25፥5-10)

Selah
PAUSE · REFLECT

- የትዕማር ባሎች ኤር እና ኦናን ለምን/እንዴት ሞቱ?

- ይሁዳ ለትዕማር እና ለቤተሰቡ የነበረው ኃላፊነት ምን ነበር?

- በቁጥር 11 መጨረሻ ላይ የትዕማር አጣብቂኝ ምን ነበር? እንደገና ማግባት ትችላለችን?

- የይሁዳ ኀጢአቶች ምን ነበሩ? በእነሱስ ማን ማን ተጎዳ?

- ኀጢአት በእግዚአብሔር ዘንድ ለምን አስጸያፊ ሆነ? (ዕብራውያን 3፥12-14)

**ዘፍጥረት 38፥12-30**

- ትዕማር በቁጥር 12-14 ውስጥ እርምጃ እንድትወስድ ያነሳሳት ምንድን ነው? ምንስ ነው ያደረገችው?

- ይሁዳ ስለ ትዕማር እርግዝና ዜና ሲሰማ ምን የተሰማው ይመስላችኋል? ምንስ አደረገ?

- እውነቱ ሲገለጥ የይሁዳ ምላሽ ምን ነበር?

- ትዕማር አታላዩን ይሁዳን ለማታለል ዕቅድ አወጣች፣ ፈጸመችውም። ዕቅዷ ምን ነበር? ስለ እርሱስ ምን ይሰማዎታል (ከቁ 17-19)? አታላይ መሆን ትክክል ነው? የትዕማር ድርጊቶች “ጻድቅ” ሊባሉ የሚችሉት እንዴት ነው?

# የአሰላስሎት ጥያቄዎች

ለትዕማር ከክፉ ባል ጋር መኖር ምን ይመስል ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ- ከክፋቱ የተነሳ እግዚአብሔር የገደለው ባል? እንደዚህ ዓይነት የሚያሰቃዩ የቤተሰብ ሁኔታዎችን መቋቋም የሚችሉበትን መንገዶች ያስቡ።
**የጥሞና ጥቅሶች ኢዮብ 1፥20-22፣ መዝሙር 16፥8፣ ኢሳይያስ 43፥1-3**

---

የትዕማርን መበለትነት ወይም ልጅ መናፈቋን በምን መንገድ በዙሪያችን እናየዋለን? የዚህ ጥያቄ መልስ በዙሪያዎ ስላሉ የተጎዱ እህቶች ሊያሳስብዎት ይችላል። ለእነዚህ ሴቶች ለመጸለይ እና ለማገልገል ልዩ ዕድሎችን እንዲሰጥዎ እግዚአብሔርን ይጠይቁ።

---

በእግዚአብሔር አስደናቂ ጸጋ እና ይቅር ባይነት ትዕማርን የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ዘር አካል እንድትሆን መርጧል። በትዕማር ሕይወት ውስጥ የእግዚአብሔርን ጥልቅ ጸጋ እና ምህረት እናያለን፣ እናም እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር እንዴት አብሮ እንደሰራም እንመለከታለን። በጌታ ሁሉን አዋቂነት እና ጸጋ ላይ ትንሽ እናሰላስል።
**የጥሞና ጥቅስ 1 ቆሮንቶስ 1፥26-31**

Selah
PAUSE · REFLECT

# አሰላስሎት



Selah

PAUSE • REFLECT

# ጥበብ

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤ የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።

መዝሙር 19:7

**ሁሉንም የሴላ ጥበብ ጥናቶች ለማግኘት**

www.selahethiopia.org/studies